# ይፋዊ ማስታወቂያ
# የኤምሪቪል ከተማ
# ዝቅተኛ ክፍያ እና የሚከፈልበት የህመም ፈቃድ

ኤምሪቪል የማዘጋጃ ቤት ህግ፣ ምእራፍ 37 ርእሰ አንቀጽ 5

**የሚጸናበት ቀን ጁላይ 1/ 2025**

## የኤምሪቪል ከተማ ዝቅተኛ ክፍያ፦

**በሰአት 19.90 ዶላር (ለትንሽና ትልልቅ ንግድ ድርጅቶች)**

ከጁላይ 1/ 2025 ጀምሮ፣ በኤምሪቪል ጂኦግራፊያዊ ወሰኖች ውስጥ በስራ ሳምንት ውስጥ ቢያንስ ለሁለት ሰአታት የሚሰሩ ሰራተኞች ከላይ ከተወሰነው ክፍያ በታች ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም።

**የዝቅተኛ ክፍያ መስፈርት**

የኤምሪቪል ዝቅትኛ የክፍያ መስፈርት የሚተገበረው በኤምሪቪል ከተማ ውስጥ ለሚሰራ ለማንኛውም ሰራተኛ (በትርፍ ግዜ፣ ሙሉ ግዜ፣ ቋሚ) ላይ ነው። በሸማቾች የዋጋ መጠቆሚያ (CPI) መሰረት በየአመቱ ከጁላይ 1 ጀምሮ ዝቅተኛው የክፍያ መጠን የሚጨምር ሲሆን ይህም በመንግስት የሚወሰን የኑሮ ውድነት ማስተካከያ ነው።

**የሚከፈልበት የህመም ፈቃድ መስፈርቶች**

የኤምሪቪል የማዘጋጃ ቤት ህግ ክፍል 5-37.03 ተከትሎ፣ ሁሉም አሰሪዎች በኤምሪቪል ከተማ ጂኦግራፊያዊ ወሰኖች ውስጥ በስራ ሳምንት ውስጥ ቢያንስ ሁለት ሰአታት ለሚሰራ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ (የትርፍ ሰዓት፣ የሙሉ ሰዓት፣ ጊዜያዊ) የሚከፈልበት የህመም ፈቃድ (PSL) መስጠት ይኖርባቸዋል።

አሠሪዎች ለትንንሽ የንግድ ድርጅቶች በየአመቱ የሥራ ጊዜ ከ 48 ሰአታት **ያላነሰ** የህመም ፈቃድ መስጠት ያለባቸው ሲሆን ለትላልቅ የንግድ ድርጅቶች ደግሞ በአመት ወይም በ 12 ወር ግዜ ውስጥ ከ 72 ሰአታት **ያላነሰ** የህመም ፈቃድ መስጠት አለባቸው። ለሠራተኞች የተጠራቀመ የሚከፈልበት የህመም ፈቃድ ከአመት ወደ አመት ሊተላለፍ ቢችልም ከላይ በተጠቀሰው ዝቅተኛ መጠን መሰረት የሚገደብ ይሆናል። አሰሪዎች በተጠራቀሙ ሰዓታት ላይ ከፍተኛውን መጠን ሊያስቀምጡ ወይም ምንም ላያስቀምጡ ይችላሉ።

ሰራተኛው የትዳር አጋር ወይም የተመዘገበ የቤተሰብ አባል ባይኖረውም እንኳ የተሰየመ ግለሰብን ጨምሮ ሰራተኞች ለራሳቸው የሕክምና እንክብካቤ ለመስጠት ወይም “የቤተሰብ አባልን” ለመንከባከብ PSL ን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ሰራተኞች ለሚመራ ውሻ፣ ምልክት ለሚሰጥ ውሻ፣ ወይም አገልግሎት ለሚሰጥ ውሻ፣ ለሰራተኛው፣ ለሰራተኛው የቤተሰብ አባል ወይም በሰራተኛው ለተሰየመ ሰው እንክ ብካቤን ለመስጠት PSL ሊጠቀሙ ይችላለሉ። አሰሪዎች ሠራተኞች የPSL ሰዓታትን ለመጠቀም የትዳር ጓደኛቸውን ወይም የሀገር ውስጥ

አጋራቸውን ምትክ የሚሆንን ሰው ለመሰየም ሠራተኛው PSL ማከማቸት ከሚጀምርበት ቀን ጀምሮ በ30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ለሠራተኞች ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ሰራተኞች አንድን ግለሰብ ለመሰየም የሚፈልጉ ከሆነ በአሰሪያቸው ከተነገራቸው በ 14 የስራ ቀናት ውስጥ መሰየም አለባቸው።

**የበቀል እርምጃ የለም**

በከተማው የተቀመጠውን ዝቅተኛ የክፍያ መጠን እና የ PSL ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት መብታቸውን የሚያረጋግጡ ሰራተኞች ከአጸፋዊ እርምጃ የተጠበቁ ናቸው። አሰሪዎች ይህንን ህግ የሚጻረር ማንኛውንም አይነት ጥሰት ካደረጉ ሰራተኞች የፍትሐ ብሔር ክስ ማቅረብ እና ተመላሽ ክፍያን፣ ወደ ቀድሞ የስራ ቦታ መመለስን እና/ወይም የእገዳ ትዕዛዝን በመጠየቅ መፍትሄ ሊያገኙ ይችላሉ። ሰራተኞች በተጨማሪም ለከተማው ቅሬታቸውን ሊያስገቡ ይችላሉ። ከተማው የዝቅተኛ የክፍያ መጠን እና የሚከፈልበት የህመም ፈቃድ አዋጅ ጥሰቶችን ሊመረምርና ሊስፈጽም ይችላል። አዋጁን መተላለፍ በገንዘብ መቀጮ እና ቅጣቶችን ያስከትላል።

ማንኛውም አይነት ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ ወይም በተገቢው መንገድ እየተከፈሉ እንዳልሆነ ወይም የሚገባዎትን PSL እንዳልተሰጠዎት ካመኑ እባክዎን በሚከተለው አድራሻ ኤምሪቪል ከተማን ያግኙ፡-

**የኤምሪቪል ከተማ**
**1333 Park Avenue**
**Emeryville, CA 94608**
**ስልክ**፡- **(510) 596-4351**
**ኢሜይል**፡- **minwage@emeryville.org**

*"ይህንን ይፋዊ ማስታወቂያ በመፈረምዎ፣ የኤምሪቪልን ከተማ ዝቅተኛ የክፍያ መጠን እና የሚከፈልበት የህመም ፈቃድ አዋጅን አንብቤ በአግባቡ ተገንዝቤአለሁ።"*

______________________________ ______________________________

***የሰራተኛ ፊርማ*** ***የሰራተኛ ስም***

____________________________________

***ቀን***